# የቅዱሳት መጽሐፍት ሥልጣናዊነት፡-

***ከነቢዩ ኢሳይያስ*** *roleneb@yahoo,com*



ውድ ተደራሲያኖቼ በዛሬው መጣጥፌ ደግሞ ስለ መጽሓፍ ቅዱስ ሥልጣናዊነትና ስለ ግል ልምምዳችን ጥቂት ነገር ላካፍላቹ መልካም ሆኖ ታይቶኛል። የየአንዳንዱን ግለሰብም ሆነ የቤተ ክርስቲያንን የሕይወት ልምምድ የመግዛትና የማስተዳደር ሥልጣን ያለው መጽሓፍ ቅዱስ ነው። ለመጽሓፍ ቅዱስ ሥልጣን ልንገዛ የምንችለው ይህንን ስናውቅ ብቻ ነው። እንደ አሁኑ ዘመን ሳይሆን ከዚህ ቀደም ባሉት ዘመናት መጽሓፍ ቅዱስ ፍጹም ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ይታመን ነበር፣ ከዚህም የተነሳ ሰዎች ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ይገዙና የሕይወትንም ሆነ የአገልግሎት ልምምዳቸውን በእግዚአብሔር ቃል ይፈትሹ ነበር። በዚህ ድህረ ዘመናይ ዓለም ግን የአንፃራዊነት አመለካከትና የሰው የግል ልምምድ እያየለ በመምጣቱ የመጽሓፍ ቅዱስ ሥልጣናዊነት የተለያዩ ተግዳሮቶች እየገጠሙት እንዳለ ማስተዋል ይቻላል ።

ባለንበት ዘመን ከቤተ ክርስቲያን ውጭ የሚገኙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በማጣጣላቸው እንደ አዋቂ የሚታዩበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። የዚህ ምክንያቱ የሰው ልክ ያጣ ደፋርነት እንደ ጥበብ እየታየ መምጣቱ ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ ሌሎች መጽሓፍ ቅዱስን በሥነ ጽሑፋዊ ውበቱ፣ በታሪካዊ ሰነድነቱና በውጤታማ ሥነ ምግባር አስተማሪነቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ድንቅ መጽሓፍ እንደ ሆነ ቢቀበሉትም፣ ነገር ግን ለድነትና ለሕይወት መለወጥ አስፈላጊ እንደሆነ አይቀበሉም ። ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ በእነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ሥልጣኑን ውሱን አድርጎታል።

ወደ ወንጌላውያን አማኞች ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ደግሞ ምዕመናንም ሆኑ አገልጋዬች ከእግዚአብሔር ቃል ሥልጣናዊነት ይልቅ በመንፈሳዊ ስጦታዎች ሆነ በጸሎት ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ አገኘነው ለሚሉት ልምምድ ተገዥ በመሆን፣ ለእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ያለመገዛት ልምምድ ይታያባቸዋል።አንዳንድ ወገኞች ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ የሆነ እንግዳና አደናጋሪ

መንፈሳዊ መረዳትና ልምምድ አላቸው። ወደ እንደዚህ ዓይነት ሕይወት ውስጥ የሚገቡት የቃሉ እውቀት ስለሌላቸውና ለቃሉ ሥልጣን የሚገዛ ማንነት ስለሌላቸው ይሆናል። ነገር ግን የተሳሳተ መረዳትና ልምምዳቸውን በቃሉ ሥልጣን ለማረም በሚፈለግበት ጊዜ ተሳስተው ላለመገኘት ሲባል ብቻ፣ እያደረጉ ያሉትን ነገር መንፈስ ቅዱስ የገለጠልኝና ያለማመደኝ ነገር ነው በማለት ልምምዳቸውን ከቃሉ ሥልጣን በላይ በማድረግ ያቀርባሉ።

እዚህ ላይ እያደረጉ ያለት ነገር ትክክል ነው በማለት እንደ ምሥክር የሚያቀርቡት መንፈስ ቅዱስ ለውስጤ መስክሮልኛል የሚለውን ሕሊናዊ (subjective) አስተሳሰብ ነው፤ ነገር ግን የቃሉ ደራሲ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ከቃሉ ጋር የሚፃረር ወይም የሚቃረን ነገር አያደርግም። አንድ ክርስቲያን ከቃሉ ሥልጣን ጋር የሚቃረን ነገር እያደረገ የክርስቲያናዊ እምነት ልምምድ ነው ቢል፣ ሳያውቀው ሌላ ኃይማኖት ሊፈጥር ይችላል። የእውነተኛው ክርስትና እምነትና ልምምድ ለቃሉ ሥልጣን የሚገዛ እንጂ ከቃሉ ሥልጣን ጋር የሚቃረን( የሚያፈነግጥ) አይደለም ።

እግዚአብሔር ለዚህ ዓለም ራሱን የገለጠውም ሆነ የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት የሚሠራው በቅዱስ ቃሉ አማካይነት ነው ( ኤፌ 5፣ 25- 27)። ቤተ ክርስቲያን ሕይወቷና አገልግሎቷ የቀናና የተሳካ የሚሆነው ለቃሉ ሥልጣን የሚገዛ ማንነት ሲኖራት ነው። በተሓድሶውያኑ የእምነት አቋም የእግዚአብሔር ቃል በቤተ ክርስቲያን ሕይወት(በትምህርቷ፣ በኑሮዋ፣ በምግባሯና በአስተዳደሯ ማለት ይቻላል) የመጨረሻው ባለ ሥልጣን ነው የሚል ነበር። በዚህ ዘመን ያለችው ቤተ ክርስቲያን ይህ አቋም የእርሷም አቋም ካልሆነ ተሸርሽራ ለማለቅም ሆነ፣ የቃሉን ሥልጣን የረገጠ ሌላ ኀይማኖት ለመፍጠር ቅርብ ነች። ቁም ነገሩ መጽሐፉን ማንበብ ሳይሆን መጽሓፍ እንደሚለው መኖርና ለሥልጣኑም መገዛት ነው። መጽሐፉ እየተነበበ የመጽሓፉን ተቃራኒ ፍልስፍና ማራመድና ተቃራኒ ሕይወት መኖርና የተለመደ ነው።

በአንድ ወቅት ጉድ ኒውስ በሚል ርዕስ በሚዚሪን ሉትረን ቤተ ክርስቲያን እየታተመ የሚሰራጭ መጽሔት አነብ ነበር። በመጽሔቱ ላይ በዓለማቀፋዊቱ የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ተፈጥሮ የነበረው መከፋፈል ሠፊ ሽፋን ተሰጥቶታል። የመከፋፈሉ ምክንያት የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ዋና መሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሥልጣናዊነት በግልጽ በመካድ ግብረ ሰዶማዊ ጳጳስ መሾማቸው ነበር። በተፈጠረው መከፋፈል ውስጥ ወግ አጥባቂዎቹ የነገረ- መለኮት ምሁራን ሹመቱን አጥብቀው ይቃወሙ የነበረው የእግዚአብሔር ቃል ስለ ግብረ - ሰዶማዊነት የሚናገረውን ቀጥተኛ ነገር በግልጽ በመናገር ሲሆን፣ ሹመቱን ለማጽደቅ የተነሱት ለዘብተኛ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ግን ነገሩን አደረግነው የሚሉት መንፈስ ቅዱስ መርቶን ነው በሚል ነበር።

በዚህ ጉዳይ ላይ በዋሽንግተን ዲሲ የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን አገረ ስብከት ዋና መሪ የሆኑት ጳጳስ ብርይንሰን ቼኒ ሰኔ 9 ቀን 2003 ዓ.ም በድረ ገጽ ባሰራጩት ጽሑፍ ለግብረ ሰዶማዊው ጌኒ ሮቢንሰን የጵጵስና ማዕረግ መስጠት የመንፈስ ቅዱስ ቀጥተኛ የሥራ ውጤት ሆኖ አግኝተነዋል። ስለዚህ ይህንን የጵጵስና ሥልጣን ያለ መቀበልም ሆነ መቃወም መንፈስ ቅዱስን መገዳደር ነው ሲሉ ገልጸዋል። በመጨረሻም እያንዳንዱ አገረ ስብከት የራሱስን ጳጳስ የመሾም መብትና ለመንፈስ ቅዱስም ሥራ ክፍት የመሆን፣ ሥልጣን አለው በማለት ተናግረዋል[1]።

እዚህ ላይ አንድ መሠረታዊ ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይሆናል። ይኸውም እነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግብረ ሰዶማዊውን ጌኒ ሮቢንሰንን ጳጳስ አድርጎ ለመሾም እንዴት ተነሱ? የሚለው ነው።የአንግሊካንን ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ለመከፈል የደረሰው ችግር ምክንያቱ መሪዎቹ የእግዚአብሔርን ቃል ሥልጣናዊነት በመካድ መንፈስ ቅዱስ መርቶናል የሚሉት አባባል ነው። መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን የሚመራት በቃሉ ስለሆነ ከቃሉ ጋር የሚቃረን ነገር አያደርግም። መገለጥ እንኳን ቢሰጠን ቃሉን የሚያጸና እንጂ የሚያፈርስ አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተሓድሶን አባቶች የእግዚአብሔር ቃል የመንፈስ ቅዱስ የመገለጫ መንገድ ነው የሚል ትምህርት ነበራቸው። መንፈስ ቅዱስን ከቃሉ ሥልጣን መለየት ኑፋቄ ነው።

---

[1] Good news No. 19 p 8

ወደ አገራችን  ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መለስ ስንል ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውጭ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል ለመሠረተ እምነት የመጨረሻና የተሟላ ምንጭ ነው ተብሎ አይታመንም። ከመጽሓፍ ቅዱስ በተጨማሪ የተቀደሱ ልማዶች መወሰን እንዳለባቸው ይታመናል[2]። በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ምዕመናን ሕይወት ውስጥ ለሚታየው የአስተምህሮና የክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ችግር ምክንያቱ ቃለ እግዚአብሔር ከምስባኩና ተነስቶ በስፍራው (በምትኩ) ሥልጣናዊ ያልሆኑ መጽሓፍት በመተካታቸውና መጽሓፍ ቅዱስን ከሥልጣኑ ዝቅ በማድረጋቸው ነው። እስትንፋሰ መለኮት ያልሆኑ መጽሓፍ ሕይወትን ለመለወጥና የሰዎችን ሕይወት በጽድቅና በቅድስና የመሙላት አቅም የላቸውም።

የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በ1992 ዓ.ም ለመጨረሻ ጊዜ ባወጣችው የክርስትና ትምህርት( ካታኪዝም) የእግዚአብሔር ቃልና ባህል  በእኩል ደረጃ ተቀባይነት ሊኖራቸው ይገባል ብላለች። በዚች ቤተ ክርስቲያን ምክር ቤት የጳጳሱ ቃል ከእግዚአብሔር ቃል በላይ ሥልጣን አለው። ቤተ ክርስቲያኒቱም ትርጉም ካልሰጠች በቀር ማንኛውም አባል የእግዚአብሔርን ቃል መተርጎም አይችልም[3]።

ወደ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያና ስንመጣ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ ማስተማር ሲገባል፣ ቃሉን በልምምዳችንና በሌሎች ርባና የለሽ ተረት ተረቶች ተክተናል። በዚህ ዘመን በቃሉ ስብከትና ትምህርት ውስጥ ማዕከላዊውን ስፍራ በመያዝ ሠፊ ቦታ የሚሰጠው ሰዎችን ነፃ የሚያወጣው እውነት ሳይሆን፣ ኩምክናና የኮሜድያኖች ሥራ ክምችት ነው። ምዕመኑም «ተሰበከ» የሚለው የእግዚአብሔርን ቃል በመንተራስ የሚያስቁት ሰባኪዎች ሲያስቁት እንጂ የክርስቶስ ባለ ጠግነት በቤተ ክርስቲያን ሲሰበክ አይደለም። ከዚህ የተነሳ ስብከቱም እየተሰበከ፣ መዝሙሩም እየተዘመረና ጸሎቱም እየተጸለየ ሰው በባህሪው አይለወጠም። ከቅዱሳን ሕይወት የሚጠበቀው ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ዐይነ ተኩላው ( ድራሹ) ጠፍቷል። በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የጳጳሱ ቃል የእግዚአብሔርን ቃል ሥልጣን ጋርዷል፤ ወንጌላውያን አማኞች ጋር ደግሞ ልምምድ።

በየአብያተ ክርስቲያኑ አዘውትረን እንኄዳለን፤ ከመድረኩ ላይ አዘውትረን የሰማነው መልዕክት ግን የወንጌሉን ሙሉ መልዕክት ሳይሆን ጎዶሎ መልዕክት ነው።ከዚህም የተነሳ የክርስትና ተብሎ የሚኖረውም የሕይወት ዓይነት መስቀል አልባና ጎዶሎ ክርስትና ነው። ምናልባት ለዚህ ዓይነተና ምሳሌ መጥቀስ ታስፈልግ ይሆናል።ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ያለው ሐሜት፤ጥላቻ፣ አጥፍቶታተ ስም/ የሰውን ስም ማጠልሸት(Character assassination)መስቀል ያልሞረደው ጠባይ፣ የእግዚአብሔር ቃል ትምህርትና ሕሊና የማይዳኜው ፈንጠዝያና ዝላይ፣ የሥነ ምግባርን ሕግ የሚጻረር ትምህርትና መርሆ አልባ ኑሮ ፣እንዲሁም እርቅ የማይፈታው ጥላቻና አፍቅሮተ ነዋይ  ነው ቢባል ማጋነን አይሆንብንም።

ከሞራል አኳያ ብዙ ነቀፊታዎች ይታዩብናል። ማራኪ ነገር( ለዚህ ዓለም የብርሃንና ጨውነት ሕይወት ማለት ይቻላል) የማይታይብን ሰዎች ሆነናል። በዚህ ምክንያት ክርስትና ገበያተኛ እንደሌለው ዕቃ ዓይነት እየሆነ መጥቷል። የዚህ ምክንያቱ ከቤተ ክርስቲያን መድረክ ከጊዜ ወደ ጊዜ ንጽህ ክርስቲያናዊ ትምህርት እየታጣ መምጣቱ ፣ የመጽሓፍ ቅዱስ ሥልጣናዊነት እየተገፋና የአዲሱ የወንጌል ንግድ ትርፋማነት(commcial Evangelim) ሥርዐት በቤተ ክርስቲያን እየተንሰራፋ መመጣቱ ይመስለኛል። አሁን ባለንበት ዘመን በአብዛናዎቹ የወንጌል አገልጋዬች ማለት ይቻላል ለእግዚአብሔር ቃል ትምህርትና ለምግባራዊ ሕይወት ግድ የላቸውም። ጉዳዩ «የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው» የሚለው የአባቶች ብሂል ዐይነት ነው። ገንዘብ ገዥ እየሆነ በመጣበት የቤተ ክርስቲያን ዓለም እግዚአብሔር በሥልጣናዊ ቃሉ የቤተ ክርስቲያኑን ሕይወት ይገዛል ማለት ዘበት ነው። አማኞች ሕይወታችንና አመለካከታችን በእግዚአብሔር ቃል እውነት መለወጥ አለበት። ይህ ካልሆነ ግን በቅዱስ ሕይወት የመመላለስ ችግር ሊገጥመን ይችላል። ከዚያ በፊት ግን ችግራችን የእግዚአብሔርን ቃል አቃልለን ከመመልከት የሚመጣ ነውና ራሳችንን በእግዚአብሔር ቃል ብርሃል እንመለከት።

እኛ ከመኖራችን በፊት በራሱ ሕልውና ይኖር የነበረ እግዚአብሔር ብቻ ነው።  እርሱ በሥልጣኑ የማይታየውን ነገር ሁሉ ወደማኖር አምጥቷል። ይህንንም ሥልጣኑን የገለጸው በልዩ ልዩ ወኪሎቹ በኩል ሳይሆን፣በሕያው ቃሉ አማካይነት ነው።

---

[2] Good news No 7p16
[3] ዝኒ ከማሁ

ይህም  ሕያው ቃል ባለ ሥልጣን ነው የምንልበት ምክንያት መገኛው እግዚአብሔር በመሆኑ ነው። ምን ጊዜም ቢሆን በሚበልጠው ላይ የሚሰለጥን ባለ ሥልጣን ነው። እግዚአብሔር በሁሉም ላይ ባለ ስልጣን ስለሆነ የመጨረሻው ባለ ሥልጣን የእግዚአብሔር ቃል ነው። ለዚህ ሥልጣናዊ ቃል የሚገዛ ማንነት ሲኖረን፣ በአገልግሎታችንም ሆነ በምንኖረው ሕይወት ውጤታሞች እንሆናለን። እንደ እውነቱ ከሆነ ልምምዳችን ከእግዚአብሔር ቃል ትምህርት ጋር የማይቃረንና የማይጣረስ መሆን አለበት ። ለእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን የማይገዛ ልምምድ በግልም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ተፋልሶን ያመጣል። እግዚአብሔር ቃሉ በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በግል ሕይወታችን ማዕከላዊ እንዲሆን የፈቀደበት ምክንያት አለ። ይኸውም የቤተ ክርስቲያንንም ሆነ የግል ሕይወታችንን የሚሠራበት አንድና አንድ ወይም ብቸኛ መንገድ ቃሉ በመሆኑ ነው።

ቀደም ብዬ ለማንሳት እንደሞከርኩት በወንጌላውያን አማኞች ዘሪያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ይልቅ የግል ልምምዶችን ከቅዱሳት መጽሐፍት ሥልጣን የበላይ አድርጎ የመመልከት አባዜ ይስተዋላል። ወደ ሌሎቹም አብያተ ክርስቲያናት ስንመጣ፣ ወግና ባህል ከአገራዊ ስሜት ጋር ተደርቦ የቅዱሳት መጽሐፍትን ሥልጣን ይዘው በጦርነት ላይ እንዳሉ እንመለከታለን ። በእነዚህና እነዚህን በመሳሰሉ አመለካከቶች  በእኛ በክርስቲያኖቹ መካከል ( የውጭውን ሳንዳስስ)የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ብርቱ ተግዳሮቶች ገጥሞታል ማለት እንችላለን። የፈለገው ዓይነት ተግዳሮት ይነሳ እንጂ፣ ዛሬም መጽሐፍ ቅዱስ በሰው ሕይወትና ምግባር ላይ ባለ ሥልጣን ነው። በዚሁ መልኩም ለዘላለም ይቀጥላል ። መጽሐፍ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት የበላይ ገዥ ነው። እንዲህ ስንል በቤተ ክርስቲያን አመራር፣ በጋራም ሆነ በየአንዳንዳችን ሥነ ምግባር  ላይ፣ በአገልግሎታችንና በመንፈሳዊ ሥጦታዎች ላይ፣ በቤተ ክርስቲያን ቶውፊት፣ በአጠቃላይ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ላይ ባለ ሙሉ ሥልጣን ነው ማለታችን ነው **(ኤፌ: 2፣19-20፣ ራ□ 2፣4-5፣ 2፣ 14-16፣ 2፣20)**::እዚህ ላይ ሓሳባችንን ከማጠቃለላችን በፊት አንድ ልብ ልንለው የሚገባ ነገር አለ ።ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ቀዳማይ ዓላማ፣ እግዚአብሔር ራሱን ለመላው የሰው ዘር በበቂ ሁኔታ በመግለጽ፣ ሰዎች  ሁሉ ያለ ምንም መደናገር የነፍሳቸው ጠባቂና እረኛ  ወደ  ሆነው ወደ አዳኙ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማስጠጋት መሆኑ ነው ( ዩሐ 14፣ 4 ፤ 2ጢሞ 3፣ 14- 17)።

ቸር እንሰንብት !

ሻሎም